“የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትምና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፥ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተወሰረ ፍጥረት የለም።
(ዕብራውያን 4፡-12)

የልጅነት ዕድሜዬን ወደኋላ ስመለከት መንፈሳዊ ድርጊቶቼ በሙሉ የተመሠረቱት ወላጆቼ የሚያደርጉት በማየት ላይ ነበር። እነርሱም የነሱን ወላጆች እያዩ እንደተማሩ አውቃለሁኝ። እንደ አብዛኞቻችሁም ይህ ለምን ይደረጋል በማለት ለመጠየቅና መረጃ ለማግኘት አልሞከርኩም። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሥርዓት እንደሆነ የታወቀ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ትምህርትና ትዕዛዛትን ከካህናት እና ከቤተ ክርስቲያንም ያገኙ እንደነበረ እርግጥ ነው።

በቅርብ ጊዜ አንድ ያስገረመኝ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በስፋት ለማሰራጨት በአማሪኛ የታተመው በአፄ ኃይለሥላሤ ዘመነ መንግሥት እንደነበር ነው። ይህ ማለት 100 ዓመት እንኳን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማኞች እጅ የገባው። ይህ የሚያሳየው በአንድ በኩል የአብዛኛው ሕዝብ የማንበብ ችሎታ (መሃይምነት) እንዳለ ሆኖ፤ አማኞች ለእምነታቸው ምንጭ በካህናት እና በቤተ ክርስቲያን ከሚሰጠው ትምህርትና መልእክት ውጭ ሌላ ምንጭ እንዳልነበራቸው ነው።

በእርግጥ ይህ ክስተት ከመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዓመታት እምብዛም የተለየ ላይሆን ይችላል። በዚያን ጊዜም ቅዱስ መጻሕፍት (የብሉይ ኪዳን እና የተወሰኑት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት) ቅጂዎች ጥቂት ነበሩ፣ ከዚያም በላይ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጊዜም በአገልጋዮቹ አማካኝነት ለምእመኑ ይነበቡ እንደነበር ታሪክ ይዘግባል። ዋናው ልዩነት ከቅዱስ መጻሕፍት (ብሉይና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት) በስተቀረ ሌሎች መጻሕፍት ለምሳሌ ተአምረ ማርያም ወይም መልከ ሚካኤል እንደ ትምህርታዊ መጻሕፍት አይነበቡም ነበር። ምክንያቱም እነዚህ መጻሕፍት ከአምስተኛው/ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የመጡ ጽሑፎች ከመሆናቸውም በላይ፣ ጸሎት ወይም ቅዳሴ ወደ ቅዱሳን፣ መላእክት ወይም ወደ ማርያም በምንም ዓይነት መልኩ አይካሄድም ነበርና ነው።

ከላይ የተመለከተውን ሃሳብ ያስቀመጥኩት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት በተወሰኑ ግለሰቦች ዘንድ ብቻ የተወሰነ ከመሆኑም ባሻገር ምእመናን እራሳቸው በቀላሉ መጽሐፍ ቅዱስን ማግኘት ይቸገሩ እንደነበረ ለማስገንዘብ ነው።

ይህ ለክርስቲያኖች ለምን ጠቃሚ ሆነ? ምክንያቱም ከብዙ ዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ገልጬ ማንበብ በጀመርኩኝ ጊዜ የተሰማኝ ልዩ ስሜት ከውስጤ ስለማይረሳኝ ነው። አንዳንዶቹ ‘አሃ!’ የሚያሰኙ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ‘እንዴ?’ የሚያስብሉ ግኝቶች ነበሩ። ማንም ክርስቲያን ነኝ የሚል ግለሰብ ሊክደው የማይችለው እውነት ቢኖር የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ያለው እና በሰውነት ውስጥ የሚያምና የሚቆነጥጥ ቀዶ ጥገና የሚያካሄድ መሆኑን ነው። ወደ ዕብራውያን መልእክቱን የጻፈው ጸሐፊ ይህንኑ በማስረገጥ ከትቦልናል። “የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም። ” (ዕብራውያን 4፥12)

ለዚህም ነው ከተወሰኑ ዓመታት በፊት የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የእምነቴ መሠረት ምንጭ እንዲሆን የወሰንኩት። ምንም ዓይነት ነገር/ውሳኔ ቢሆን ሁል ጊዜም እግዚአብሔር/የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ላይ ምን ይላል? ይህንን ጉዳይ እግዚአብሔር/የእግዚአብሔር ቃል ይደግፈዋል? እያልኩኝ ዘውትር እጠይቃለሁኝ። መጽሐፍ ቅዱስ/የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16 ላይ ጳውሎስ የተጠቀመው የግሪክ ቃል ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የወጣ የሚል ሃሳብ የያዘውን የግሪክ ቃል theopneustos ወይም [θεόπνευστος] ነው። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ሥፍራ ዘንድ ብቻ የሚገኝ ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ምንጭና አማኞችን የሚቀድስ መለኮታዊ ኃይል ያለው መሆኑን የሚያስረግጥ ቃል ነው።

ስለዚህ በምንም ዓያነት ሁኔታ፣ ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል/መጽሐፍ ቅዱስን በትንሹም ሆነ በትልቁ የሚቃረን፣ የሚቃወም ምንም ዓይነት ነገር፥ ሥርዓት፣ የእምነት አቋም፣ አዝማሚያ ቢኖር በጥንቃቄ ልንገመግመው ይገባል። ይህ የእምነት አቋም፣ ትምህርት፣ ሥርዓት ወይም ትውፊት እግዚአብሔር ከደነገገው ከአንደበቱ ከወጣው ከቃሉ እውነት ዘምበል እንኳ ቢል ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም። ውድቅ/ውግዝ መሆን አለበት። ምንም እንኳን ትምህርቱን ወይም ትውፊቱን የሚያስፋፋው ወይም የሚደግፈው ጳጳሱ፣ ፓትሪያርኩ፣ ፓስተሩ ወይም ተራው ምዕመኑ ቢሆኑ ማንም ከእግዚአብሔር በላይ ሊሆን አይችልምና። እንደዚሁ ተማርን የሚሉቱ ሳይንቲስቶች፣ ሳይኮሎጂስቶች ወይም የኒው ኤጁ ጉሩዎችም ቢሆኑ ትምህርታቸውና አቋማቸው ሊወገዝ ይገባል። ማንም፣ ምንም ከእግዚአብሔር እስትንፋስ Theopneustos ጋር ሊወዳደር አይቻለውም!

የእምነትሽ/ህ መሠረት ምንጭ ምንድነው?